# በፀረ መለስነት ሽፋን ወያኔነት ሲውገረገር

# ከገብሩ እስከ ስዬና አስገደ

ገመቹ ሀብተ ማርያም

ፀሀፊው ራሱን አስገደ ገብረ ሥላሴ ነኝ ብሏል፡፡ የቆየ የተሓህት/ሕወሓት አባል፣ መስራች መሪ ነው/ነበር፡፡ የመፅሀፉ ስም ጋህዲ የሚል ነው፡፡ በገሀድ በይፋ ታየ ታወቀ / ይታወቅ ለማለት መሰለኝ፡፡ አቶ አስገደ የዘሬን ብተው ይዘርዝረኝ ዓይነት ከመሰረታዊ ወያኔያዊ ጠባብነቱ ጋር በሙጥኝ ተቃቅፎ ይህ የፃፈው መፅሀፍ በፀረ መለስ ሽፋን ወያኔነትን ለሚያቀነቅኑ የሚያስደስት ሆኗል፡፡ በጣም ያሳዝናል!!

አቶ አስገደ  የዚህ  ከይሲ ቡድን መስራች አባል ከነበረና ለዓመታትም በአመራር ቦታ በውስጥ ከነስብሐት ዓይነቶቹ ጋኔኖች ጋር ሲዶልትና በልዎ ሲል ከቆየ በእውነቱ ዛሬ ከቆጨውና ካዘነ፣ ባለፈው ድርጊቱና አቅዋሙ ከተፀፀተ በመፅሀፉ ሊያሰፍር የሚገባው ብዙ ጉድና ሀቅ ነበረ፡፡ ግን አላደረገም፡፡ የእሱን እዚህ ትተን ከእሱ ቀደም ብለው ከመለስ ጋር ተጋጨን ብለው ከወያኔ ወጣን ያሉትን የፖሊት ቢሮ/የወያኔ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ/ አባል የነበሩትን እነ ገብሩ አስራት ን፣ ተወልደን፣ አለምሰገደን እስቲ እንያቸው፡፡ ከመለስ ዜናዊ ቢጋጩም ይህ ነው የሚባል የዚያን መጥፎ ድርጅት ጉድ ለሕዝብ አላጋለጡም፡፡ የእነ ፀጋየረ ገብረ መድህን ደብተራውን እስራትና ደብዛ መጥፋት (ምናልባትምመገደል) በተመለከተ ትንፍሽ ሊሉ ይቅርና አንዳቸው ያውም የትግራይ ገዢ ተብሎ የነበረ ሳለ  የኮለኔል ቃል ክርስቶስ አባይንም መያዝ (ከዚያ በኋላ ተፈተው ዛሬ አርፈዋል) ክዶ/ክደው አናውቅም ብለው ነበር፡፡ በ06 ተይዘው ስለተፈጁ የትግራይ ዜጎች፣ ወደ ኤርትራ ተልከው በጠመንጃ ልዋጭ በናቅፋ ስላለቁ የትግራይ ወጣቶች፣ ጃሱስ ሰላይ እየተባሉ ስለተፈጁት ንፁህ ዜጎች፣  የአማራ ኮራኩር ተብለው ስለተገደሉት፣ ስለ ሐወዜን ምስጢር፣ ከዚያድ ባሬና ከሱዳን ጋር ስለነበረው ስምምነት፣ ስለ እነ ተከሉ ሐዋዝ አገዳደልና በትግራይ ነፃ አውጪ ግንባረ መሪ ወጣቶች ላይ በአይጋ ስለተፈፀመው አሰቃቂ ግድያ፣ በረሀቡ ጊዜ ከሲአይ ኤ ጋር በተደረገው ስምምነት መሰረት አቅም አልባው ሕዝብ ወደ ሱዳን እንዲጋዝ ተገዶ በወዲ ከውሊና ሌሎች ቦታዎች ስላላቁ የትግራይ አርሶ አደሮች፣ ወያኔ ወደ ስልጣን ሲጓዝ በኢሕአፓ ላይ ስለፈፀመው ግድያዎች፣ስልጣን ሲይዝ ስለፈፀማቸው ወንጀሎች  ወዘተ ለሕዝብ የገለፁት ያጋለጡት የለም፡፡ በተለይም ከሻዕቢያ ጋር ስለነበረው የተዛባ ግንኙነት ያጋለጡት የረባ ነገር የለም፡፡ በወንጀሉ ተካፋይ ነበሩና ፣ተጠያቂ ነበሩና፣አሁንም የወያኔን ጠባብ ፖለቲካና ራዕይ ከሞላ ጎደል ይጋራሉና ዝምታንና ሆድ ይፍጀውን መርጠዋል፡፡ ታዲያ የሌባ ዓይነ ደረቅ እንዲሉ ዛሬ ተቃዋሚ ነን በሚል ሽፋን ሀገር ወዳድ፣አርበኛ፣ ነፃ አውጪ የሚል ካባ ለብሰው ተጎንበሱልን፣ታዘዙን (መፅሀፍ ግዙን፣አዳንቁን) ሊሉን ተደራጅተው ተራ እየጠበቁ ናቸው፡፡

አቶ አስገደ የወያኔ ድርጅት ሀ ብሎ ሲጀምር በሰይጣናዊ የደደቢት የጠባብ ቅብዓ ርኩስ ተጠምቆ ሀገር ሊያጠፋ ሊያዋርድ መነሳቱን በመደበቅ ችግሮች ሁሉ በኋላ ወይ መለስ ስልጣን ሲይዝ ወይም መለስ እነ ገብሩና ጭፍሮቻቸውን ጭራቸውን አስቆልምሞ ከስልጣን ሲያባርር ወይም ለእስር ሲዳርግ የተፈጠረ አስመስለው ማቅረብን መርጠዋል፡፡ ወያኔ ሀ ብሎ የጥፋት ጉዞዎን ሲጀምር የትግራይን ሕዝብ ጠላት አመራ ብሎ ሰይሞ፤ መገንጠል ተገቢና አይቀሬ ነው፤ ሕዝብ አብሮ መኖር አይችልም፤ ይችላል የሚሉ የሸዋ ትምክህተኞችና እስመሳይ ተራማጆች ብቻ ናቸው ብሎአጓርቶ፤ ኢሕአፓን በትምክትኛነት አውግዞ፤ ነፃ የትግራይ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሬፑብሊክን እመሰርታለሁ ብሎ የተነሳ ነበር፡፡ ፕሮግራሙ፤መርህ ግብሩ፤ጠማሩ ማኒፌስቶው ይህ ነበር፡፡ ታዲያ ይህን ድርጅት ነው ጤነኛና ለኢትዮጵያ አሳቢ ብሎ ለማቅረብ አስገደም ሌሎችም የሚሞክሩት?ይህ ሌላ ወንጀልና ፀረ ሕዝብ ፀረ ሀቅ ሙከራ አይደለምን? የአስገደን ሙከራ አበበ በለውና አብርሃም በላይ ቢያጅቡትና ሊያዳንቁለትም ቢሞክሩ አስገራሚ አለመሆኑ እንዳለ ሆኖ ግለሰቡ ኢሕአፓን በትምክህት ሊከስ መነሳቱ ግን ምንኛ ዓይነ ደረቅ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ዛሬም በአሲምባ ኢሕአፓ ጦርነት ከፈተብን ብለው የሚቀላምዱ ተቀዋሚ ተብዬዎች የክልል 1 ፍሬዎች አሉ፡፡ ጉድ!  ትላንት ኢሕአፓን የታላቂቷ ኢትዮጵያ ትምክህተኛ ወኪልና የአማራ ድርጅት ብለው ሊያስጠሉ ሲሞክሩ የነበሩ ዛሬ ከዚሁ ከዋሾ ወያኔ ተለየን እያሉ አንደ አስገድ የተጋቱተተን ወይ ወጣቱን ሲግቱ ውሸትና ጥላቻ የሚደግሙ አሉ፡፡ ታዲያ የት ላይ ነው አስገደ ከቀጣፊውና ፀረ ኢትዮጵያው ስብሓት ነጋ የተለየው? መለስ ብቻ ሳይሆን የወያኔ ድርጅት ነው፤ አመራሩ ነው ለሻዕቢያ ያደረ፡፡ አሰብን ያስቀማ መለስ ብቻ አይደለም--ከገብሩ አስራት ጨምሮ ሌሎችንም ዛሬ ከመ ጲላጦስ ሊሆኑ የሚዳዱትንም ይመለከታል፡፡ በአንድ ግለሰብ ወይ በሁለት ሶስት ላይ ብቻ የሚጣል ወንጀል ሳይሆን አብረው በነበሩና በወሰኑት ሁሉ ላይ የሚመጣና የሚመለከታቸው ነው፡፡ ለዚህም ነው ፀረ መለስ መሆን? ፀረ ወያኔነት፤ፀረ ጠባብ መሆን አይደለም የሚባለው፡፡ አቶ አስገደ ፈተናውን ወድቋል፡፡ ትላንትም ጠባብ፤ ዛሬም በትግራዊ ጠባብነት የታጀለ ጠባብ፡፡

ወጣቱ ትውልድ ሀቀኛ ታሪክን እንዳያውቅ በዚህም በዚያም መፅሀፍ ፀሀፊና የህይወት ታሪክ ተራኪ ሆነው ብቅ ብቅ ያሉት ሐሳዊዎችን ማጋለጥና ሀቅን መጠበቅ መንከባከብ ያስፈልጋል፡፡ አስገደ እንድ ኮሾ የቀድሞ የአቃቂ ጣቂ ተተርትሯል--ጠባብነቱንና ፀረ ኢትዮጵያ ድርጅት መስርቶ ሀገራችንን መጉዳቱን ግን ራሱም ሆነ ርካሽ ጋዜጠኞች ነን ባዮች ቅጥረኞች ሊሸፍኑለት አይችሉም፡፡ አታንቡ ማለት አንድ ግብዙ መለስ መሆን ሊያስመስል ቢችልም ለአስገደ መፅሀፍ ገነዝብ ከማባከን ገንዘቡን ለፖለቲካ እስረኞች ይፈቱው ዘመቻ ማዋሉ ይመረጣል፡፡

መጥኔ ለወያኔ ጠባቦችና በወያኔ መርዝ ለተነደፉ ሁሉ!!!